# ወያኔ በዴራ ሰሜን ሸዋ ዐማራና ኦሮሞን ለማጋጨት የሸረበው ሴራ ከሸፈ፤ የ3 ሰዎች ሕይወት አልፏል

October 20, 2017

Muluken Tesfaw

በሰሜን ሸዋ ዴራ ትናንት የዐማራና የኦሮሞ ተወላጆችን ለማጋጨት በአገዛዙ የተሸረበው ሴራ ሙሉ በሙሉ የከሸፈ ቢሆን በአገዛዙ ኃይሎች የሦስት ሰዎች ሕይወት አልፏል፡፡ ትናንት ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም ከጠዋት ጀምሮ በዴራና በመራቤት የተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ተካሒደዋል፡፡

በተቃውሞ 7 ሰዎች በጥይት የተመቱ ሲሆን የሁለቱ ሕይወት ወዲያውኑ ሲያልፍ አንደኛው መራቤቴ ሆስፒታል ቢደርስም መትረፍ ባለመቻሉ የሟቾች ቁጥር ሦስት ሆኗል፡፡ ቀሪዎቹ 4ቱ ደግሞ በሪፈራል ወደ ደብረ ብርሃን ሆስፒታል ተልከዋል፡፡

የአገዛዙ ኃይሎች ከቱቲ የመጡ ዐማሮች ኦሮሞዎችን ሊያጠፉ ነው ብለው ቢሰብኩም «ሁላችንም አንድ ነን» በሚል ከመራቤቴ፣ ብቸናና ዴራ የተሰባሰቡ ዐማሮችና ኦሮሞዎች ዛሬም ከአገዛዙ ኃይሎች ጋር ሲጋፈጡ መዋላቸውን ከቦታው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡
የመራቤቴ ከተማ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢጋዚ ወታደር እንደተከከበ ምንጮች ጠቁመዋል፡፡